

# 4

# ገር መሳይ ኃጢአት “ኩራት”

## 4-1

***“ትዕቢት ጥፋትን፥ ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል”***

**ምሳሌ 16፥18**

“ኃጢአት” ማለት በአጭሩ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ወይንም ከባህሪው ውጪ መኖር ማለት ነው። የእግዚአብሔር ባህሪ መታየት የክብሩ መገለጥ ሲሆን፥ ኃጢአት ያንን ታላቅ የመገለጡን ክብር እንዳይታይ ይሸፍናል። ሰው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ሕይወቱን የሚመራ መሆኑን አንዳንድ በሚሠራቸው ተግባሮች በግልጽ ያውቃል። መሥመር የለቀቀውንም እርምጃውን “ኃጢአት” ብሎ መጥራት አያስቸግረውም። አልፎ አልፎ ግን ግልጽ ሆነው የማይታወቁ ኃጢአቶች አሉ። መልካቸውን አሳምረው የሚቀርቡ በመሆናቸው ኃጢአትነታቸውን ለይቶ ማወቅ ያስቸግራል። ጠልቆ ላልተመለከታቸው ገር ስለሚመስሉ፥ ብዙ ክርስቲያኖችን ያሳስታሉ። አጥብቆ ሊያዛቸው ሰው ከቅድስና ሕይወት ውጪ መኖሩ አይሰማውም። እንዲያውም በእነርሱ ይመካባቸዋል። እነዚህ “ገር መሳይ ኃጢአቶች” አደገኛነታቸው በግልጽ ስለማይታይ የብዙዎችን መንፈሳዊ ሕይወት አዳክመዋል። ከነዚህ ገር ከሚመስሉ ኃጢአቶች መካከል ዋነኛው “ኩራት” ወይንም ትዕቢት ነው ብንል አልተሳሳትንም። በዘመናችን “ኩራትን” እንደ መጥፎ ጠባይ በማውገዝ ፈንታ፥ እንደ መልካም ባህሪ መታየቱ ግልጽ ነው። እንደ ዘመኑ አባባል “ኩሩ” ሰው ራሱን ችሎ የሚቆም፣ ለማንም የማይንበረከክ ወይንም የማይሰግድ ነው ተብሎ ስለሚታመን እንደ መልካም ባህሪ ይደነቃል። በዚህ እምነት ሕይወቱን መምራቱ ብቻ ሳይሆን፥ በእግሩ ለሚተኩትም ልጆቹ ያስተምራል። ለራሱ እንዲስማማው ቋንቋውን ለውጦ ያቀርበዋል። “ኩራተኛ ወይንም ትዕቢተኛ ነኝ” በማለት ፈንታ “ራሴን ችዬ የምቆም፣ ለማንም የማልንበረከክ ለራሴ ክብር ያለኝ…ማንም ወደታች እንዲመለከተኝ የማልወድ ኮስታራ ወንድ ነኝ…ወዘተ” ይላል።

የዘመኑ ሰው ቋንቋውን በመለወጥ ልዝብ መስሎ እንዲታይ በማድረግ በሕይወቱ ይለማመደው እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ግን አደገኛነቱን መናገሩን አላቋረጠም። እንዲያውም እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ሰባት ነገሮች መካከል አንደኛው “ኩራት” እንደሆነ ይናገራል። በመጽሐፈ ምሳሌ 16፥18 ***“ትዕቢት ጥፋትን፣ ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል”*** ይላል።

ክርስቶስ ሰውን ሊያረክሱት የሚችሉትን ኃጢአቶች ሲዘረዝር፥ ከዘረዘራቸው መካከል “ኩራትም” ይገኝበታል። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ በዘመኑ የነበሩትን ጣኦት አምላኪ አህዛቦችን የኃጢአት ሕይወታቸውን ሲዘርዝር፥ የጠቀሰው አንደኛው ኩራትን ነው። ያዕቆብና ጴጥሮስም በመልዕክቶቻቸው “እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሁታን ግን ጸጋውን ያበዛላቸዋል” በማለት ጽፈዋል። እንግዲህ “ኩራት” ምንም ያህል ቋንቋው ወይንም መጠሪያ ስሙ ተሻሽሎ ቢቀርብም መጽሐፍ ቅዱስ የማይደግፈው ባህሪ መሆኑን መረዳት አያስቸግርም። ብዙ ጊዜ ‘ኩራት’ ምን እንደሆነ ማወቅ ያስቸግራል። “ራስን መጠበቅ…ራስን አለማዋረድ” ከሚለው ሃሳብ ጋር ሳይጋጭብን አይቀርም። በመሠረቱ ራስን መጠበቅ ክፋትነት የለውም። ጳውሎስም ጢሞቴዎስን ሲመክረው “ማንም ታናሽነትህን አይናቀው” አለው። ይህን ማለቱ “ማንም ሰው አያዋርድህ…የሚገባህን ክብር አይከልክልህ” ማለቱ ነበር። እንግዲህ ሌሎች እንዲያከብሩት የሚፈልግ ሁሉ አስቀድሞ ራሱን ማክበር እንዳለበት ግልጽ ነው። ራስን ማክበር በአግባቡ ከተረዳነው መጥፎ አይደለም። “በኃጢአት ወድቄ ራሴንና እግዚአብሔርን አላዋርድም” ማለት ብርቱነት ነው። ሰው ብዙ መስዋዕት የተደረገለት ፍጡር በመሆኑ ራሱን ሳይጠብቅ አልባሌ ቦታ መጣል የለበትም። በክርስቶስ ደም የተገዛ ፍጥሩ በመሆኑ

ለእግዚአብሔር ብቻ የቆመ መሆን አለበት። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ‘ኃጢአት” ብሎ የሚጠራው “ኩራት” እኛ እንደምንገምተው “ራስን ማክበር” አይደለም። እንዲያውም ራስን ማታለል ነው። ጳውሎስ ሊኮራባቸው የሚችልባቸው ብዙ ነገሮች ቢኖሩትም “በእነዚህ…በእነዚህ…እኮራለሁ” በማለት የዘረዘራቸው ነገሮች አልነበሩም። ጳውሎስ ሁሉንም ውድቅ አድርጎ “በወንጌል አላፍርም” አለ። ይህንን ማለቱ በወንጌል ብቻ እኮራለሁ ማለቱ ነበር። “ኩራት” ራስን ከፍ አድርጎ በማቅረብ ሌሎችን ወደታች መጫንና ዝቅ አድርጎ መመልከት፥ በራስ ትምክህት የተነሳ በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በብሉይ ኪዳን “ኩራት” ዘጠኝ የተለያየ ትርጉም እንዳለው ሆኖ ሲዘረዝር፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ በሦስት የግሪክ የተለያዩ ቃላት ተጠቅሷል።

## 1. አላዞኒያ

ይሄ አላዞኒያ በሮሜ 1፥30 እና በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥2 ላይ ተጠቅሷል። ይህ ቃል የሚጠቅሰው በተለይ በማስ መሰል የቃላት ጨዋታ በማድረግ፥ ለራሱ ጥቅም ሲል ማድረግ የማይችለውን እደሠራ ወይንም መሥራት እንደ ሚችል የሚያወራውን ሰው ነው። በዚህ ዓይነት የኩራት መንፈስ የተያዘ ሰው ታላቁን እግዚአብሔርን ችላ ብሎ በራሱ ሃሳብ ብቻ የሚመራና (2ኛ ዮሐ. 2፥16) እንዲሁም ለወደፊት ሕይወቱ መመሪያ የሚያወጣ ነው (ያዕ. 4፥16)። እግዚአብሔርን ችላ በማለት የራሱን አምባገነንነት እውነት ባልሆነ ቃል አሳምሮ የሚያወራውን በግሪክ አላዞኒያ ብሎ ይጠራዋል።

## 2. ሃይፐርፊኒያ

ኩራት የሚለውን ቃል የሚገልጽ ሁለተኛው የግሪክ ቃል ሃይፐርፊንያ የሚለው ነው። ይህ ቃል የሚጠቅሰው እራሱን ከሌሎች አስበልጦ የሚያየውን ሰው ሲሆን፥ ይሄኛው የጉራ ቃሉን በአደባባይ የሚያሰማ ወይንም የሚያ ሳይ አይደለም። በልቡ ግን ከሌሎች ሁሉ የተሻለ መስሎ ስለሚታየው የራሱን ታላቅነት የሚያመልክ ሰው ነው።

## 3. ሃይብሪስ

ሌላ ኩራትን የሚገልጽ የግሪክ ቃል ሃይብሪስ የሚለው ቃል ነው። ሃይብሪስ የሚገልጸው ከትዕቢቱ የተነሳ ከእርሱ ያንሳሉ ብሎ የሚገምታቸውን ሰዎች በኃይል ለመጉዳት የሚነሳውን ሰው ነው። ይህን ዓይነት ባህሪ ያለው ሰው ተፈጣሪንቱን ረስቶ በእግዚአብሔር ላይ የሚያምጽና ከሚገባው በላይ በራሱ ትልቅነት የሚያምን ነው። ትልቅነቱንም የሚያሳይበትና የሚያረጋግጥበትም ሌሎችን በመጉዳት ነው (2ኛ ቆሮ. 12፥10)። ኩራት ኃጢአት እንደሆነ አማኝ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶ ያነባል (1ኛ ጢሞ. 3፥6)። ኩራት ልብን የሚያስት (ኤር. 49፥16) አእምሮን የሚያደነዝዝ (ዳንኤል 5፥20) እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። የኩራት ተቃራኒ ትህትና ነው። ትህትና ደግሞ ከመንፈስ ፍሬዎች አንደኛው እንደሆነ መጽሀፍ ቅዱስ ይናገራል። ኩራት የክርስቶስ ባህሪ በአማኞች ሕይወት እንዳይታይ የሚሸፍን በመሆኑ ፍጹም ሊወገድ የሚገባው ባህሪ ነው። ኩራት የክርስቶስ ቁንጅና በክርስቲያኖች ሕይወት እንዳይታይ ከመሸፈኑም በላይ ለመንፈሳዊ አገልግሎትም ዋና እንቅፋት ነው። ፉክክርን፣ አለመተማመንን፣ ጥላቻን፣ አንዱ የሌላውን ሥራ ማሳነስን ስለሚፈጥር በህብረት ታላቅ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳይሠራ እንቅፋት ይሆናል። ኩራት ከሰው ሕይወት ተነቅሎ መውጣት ያለበት የሕይወት መርዝ ነው። ኩራት በተለይ የመንፈሳዊ ሕይወትን በመዳከም እንቅፋት የሚሆንበት ብዙ ምክንያቶች ሲኖሩት፥ ከብዙ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ሞክረናል።

**በሚቀጥለው ክፍል፥ ኩራት ለመንፈሳዊ ሕይወት እንዴት እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል እንመለከታለን።**

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**